# የትንሣኤ በዓል መልዕክት

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

## የ፳፻፱ በዓለ ትንሣኤ መልዕክት፤ በዝርወት ለአለች ቤተ ክርስቲያን፤ "ለመዳን አዳኝ"

በመጀመሪያ አዳኝ የሚለው ቃል ብዙ ትርጉም አለው ሲጠብቅ፤ ሌላ ትርጉም አለው በዚህም ወደ ፊት እንሄድበታለን። ለአሁኑ ሳይጠብቅ አዳኝ የሚለውን እናቀርባለን። (እንመለከታለን)።

፩ኛ/ በሕመም የሚሠቃይ፤

፪ኛ/ በጠላት እጅ የወደቀ፤

ለመዳን አዳኝ ለሚለው ርእሳችን በእነዚህ በተዘረዘሩት ሁለት ርእሰ አርእስት ላይ አንድ በአንድ እናተኩራለን።

### በሕመም የሚሰቃይ

የሕመም ዓይነቶች ብዙ የብዙ ብዙ ናቸው፤ በዚች አጭር ጦማር ማስፈርም ሆነ መግለጽ አይቻልም፤ ዝርዝሩን ለባለሙያዎች እተወዋለሁ። ለዛሬው አጭር ማስታወሻየ የምወስደው በአጠቃላይ በሁለት የሰውን ምንነት የሚገልጹትን ነው።

፩/ የሥጋ ደዌ

፪/ የነፍስ ደዌ።

የሥጋ ሕመም ሲባል፤ ደዌ ሥጋን የሚገልጽ ነው፤ እሱም በሦስት ነገሮች ላይ ያተኩራል፤ ሥጋዊ፤ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ደዌን (ሕመምን) ይገልጻል።

### ሀ/ ደዌ ሥጋ

ከደዌ ሥጋ መዳኛ የሚሆኑ በየአህጉራቱና በየክፍላተ ዓለሙ ታላላቅ ሆስፒታሎች ተገንብተዋል፤ የማዳን (የፈውስን) ተግባር የሚያከናውኑ ሐኪሞች ሰልጥነዋል፤ መድኃኒቶች ተቀምመዋል፤ ይህ ዓይነቱ የሥጋ ማዳኛ ድርጅት የሌላቸው ደግሞ እንደ ሀገራችን ኢትዮጵያ ያሉ በጸበል፤ በሀገር መድኃኒትና በባለመድኃኒት ይረዳሉ። በየአህጉሩና በየክፍላተ ዓለሙ ደግሞ የዚህን ዓይነት እርዳታ የማያገኙ ብዙ ናቸው፤ በተለይ ሀገራችን የሚበልጠው ክፍል ምንም ዕድል የሌለው ነው። በማህጸን እያለ የሚጨነግፈው፤ ወዲያው እንደ ተወለደ የሚሞተው፤ ተወልዶ መንቀሳቀስ ሲጀምር በለጋነቱ የሚቀጭው ትውልድ

የሚበልጠው እንደሆነ ተረጋግጧል። ወገኖቼ ለእነዚህ ወገኖቻችን ሀገሪቱን እመራለሁ የሚለው ንብረቱን የሚቆጣጠረው ክፍል ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑን ያመለክታል። ሆኖም ግን የማዳን ችሎታው ያለን ክርስቲያኖችም የሚጠበቅብንን ክርስቲያናዊ ግዴታችንን በአለመወጣታችን መብቱን በሰጠን በእግዚአብሔር ዘንድ እንጠየቃለን፤ “ታምሜ አልጠቃችሁኝም” የሚለው የፍርድ ቀን አዋጅ አለና። ወገኖቼ በዚች አጭር የመቆያ ዘመናችን ወገኖቻችን እንርዳ፤ የመጀመርያ ክርስቲያኖችን ሕይወት እንከተል፤ በእነርሱ ዘንድ ሥጋዊ ደዌና ችግር የሚባል በመካከላቸው አልነበረም፤ በዚህ አጋጣሚ በዝርወት የአለችው ቤተ ክርስቲያን የታመሙትን በመጠየቅ በመንቀሳቀስ ላይ ትገኛለች፤ “ለመዳን አዳኝ” ማለት ይህ ነው፤ ይህንን በመጀመርያ ክርስቲያኖች ሕይወት ተፈጽሟል። ዛሬም እየተፈጸመ በማየቴ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ። ይህም ጉዞ ወደ ማኅበራዊ ፈውስ የሚያደርስ አንደኛው ክፍል ነው።

## ለ/ ማኅበራዊ ደዌ

የማኅበራዊው ሕይወት ሕመም (ደዌ) እንደ ተስቦ በመዛመት በዓለማችን ተዳርሷል። ይህ ግዙፍ መስሎ የሚታየው መንግሥት የሚመሠረተው ከተለያዩ ሁለት ተቃራኒ ጾታዎች ነው። የእነዚህ ሁለት ተቃራኒ ጾታዎች ግንኙነት ቤተሰብ የሚለውን ያስገኛል። ከቤተሰብነት ወደ መንደር ከዚያም አድጎ ወደ መንግሥትነት ይለወጣል። ዓለማችን ዛሬ ከመቶዎች በላይ የሚቆጠሩ መንግሥታት፤ በቢልዮን የሚታሰቡ ሕዝቦች የሠፈሩባት ናት። ዛሬ ይህን ያህል ሕዝበ-አሕዛብ የሠፈረባት ምድራችን ወደ መንደርነት በመለወጥ ላይ ትገኛለች። ግን ምን ይሆናል ይህ ማኅበራዊ እሴት በደዌ በመጠቃት ላይ ይገኛል። በማይድን በሽታ ስለተመታ ግቢ-ነፍስ ውጪ-ነፍስ ደረጃ ደርሶ ያጣጥራል። ክርስቶስ ስለነገረ ምጽዓቱ ሲናገር “የሞት ጻዕር” ብሎታል። ዛሬ የዓለም ሕብረተሰብ እርማጌዶን እርማጌዶን እያለ ሞትን በመጥራት ተሰልፏል። ከዚህ ከተያዘበት የማኅበራዊ ደዌ የሚፈውሰው መድኃኒት፤ ባለመድኃኒት ይኖር ይሆን? አዎን አለ። “በእርግጥ እርሱ ደዌችንን ወሰደ ሕመማችንን ተሸከመ” ተብሎ በነቢዩ የተነገረለት ክርስቶስ “እናንተ ሸክማችሁ የከበዳችሁ ወደ እኔ ኑ እኔ አሳርፋችኋለሁ” እያለ የሚጣራ፤ እራሱ መድኃኒት እርሱ ራሱ ደግሞ ፈዋሽ ባለ መድኃኒት ነው። ወደ እሱ የመጣውን ሁሉ ዋጋ ሳያስከፍል በነፃ ይፈውሳል። ፈዋሹ ፈውስ ለሚፈልገው ማኅበራዊ ሕይወት ቅድመ ሁኔታዎችን ያስቀምጣል። እግዚአብሔር የለሽነትን፤ ግብረ ሰዶማዊነትን፤ አመንዝራነትን፤ እራስ ብቻ ወዳድነትን፣ በአንድ ሴት በአንድ ወንድ ጸንቶ አለመኖርን ምቀኝነትን፤ ቀናተኛነትን፤ ዋሾነትንና አስመሳይነትንና አልጠግብ ባይነትን አስወግዶ የሚቀርበው ብቻ ነው ፈውሱን የሚያገኘው። እነዚህን አስወግዶ የቀረበ ማኅበራዊ ሕይወት ይፈወሳል። በዚህ ዓይነት የሚፈወሰው ማኅበራዊ ሕይወት ረዥም ዕድሜ ይኖራል። ምድራችን ምድረ ገነት ትሆናለች። የማኅበራዊ ሕይወት ጤናማነት፤ የፖለቲካ ብክለትንም ይታደጋል።

## ሐ/ ፖለቲካዊ ደዌ

ከፖለቲካ ደዌ ለመዳን የዓለም መንግሥታት ሕይወታቸውን ሁሉ በፖለቲካ ላይ የተመሠረተ ያደርጋሉ። የፖለቲካውንም አመራር የሚይዙት ከታወቁ ማሰልጠኛዎች የወጡና የህግ ሊቃውንት፤ በፖለቲካ ሳይንስ የረቀቁ ናቸው። ሕግ አውጪ፣ ህግ አስፈጻሚ ክፍልም አላቸው። ይህ ሁሉ የሚሆነው የሰው ልጅ መልካም አስተዳደር አግኝቶ ምድራዊ ኀነት እንዲኖር ታስቦ የተደረገ ነው። ይህንንም ምዕራቡ ዓለም ተግባራዊ እንዳደርገና ሌሎችም በእሱ መርሆ እንዲመሩ የማያደርገው ቅስቀሳ የለም። ግን ፖለቲካው በደዌ ስለተበከለ እንኳን ለሌላው ሊደርስ እርሱም የማይኖርበት ዘመን እሩቅ አይደለም። ይህ የፖለቲካ ደዌ በምዕራቡ ዓለም ማደንዘዣ ሲኖረው የሦስተኛው ዓለም ሀገሮች በተለይ ኢትዮጵያን የመሰሉ ግን ምንም የላቸውም። በዚህ ምክንያት ወጣቱን ወጣቷን እየመረጠ ከገጸ ምድር እያጥፋ ይገኛል፤ በተለይ በሀገራችን የዘር የፖለቲካ ደዌ በሁሉም የደረሰ ቢሆንም በተለይ በአማራውና በኦሮሞው ሥቃዩና እልቂቱ ጎልቶ ይታያል። ለዚህ ፖለቲካዊ ደዌ መፈወሻ መድኃኒት፤ ባለመድኃኒት አለው? እንዴታ፤ አለው። በብሉይ ኪዳን የሙሴ በትር (በትረ ሙሴ)፣ የጌድዮን ፀምር፣ የኖኅ መርከብ እንደ ምሳሌ ይጠቀሳሉ፤ በሐዲስ ኪዳን ኢየሱስ የሚለው ቃል ትርጉም፤ የመድኃኒቱ አጠቃቀም "ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን እናንተም እንዲሁ አድርጉላቸው" "ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ" ፍቱን መድኃኒቶች ናቸው። በዚህ መሠረት መመራቱም መምራቱም ከአለ የፖለቲካ ደዌ ይጠፋል፤ አስተዳደሩ ሰላም የሰፈነበት፤ ዓለማችን ኀነት ተሰፋችን መንግሥተ ሰማይ ይሆናል። ነፍሳችንም የነፃነት፤ የደስታና የሰላም አየር ትተነፍሳለች።

## ፪/ የነፍስ (የመንፈስ) ደዌ፤

ነፍስ በዓይን የማትታይ በእጅ የማትዳሰስ በሚታይ በሚጨበጥና በሚዳሰስ አካል ተዋሕዳ ሰው የሚለውን ትርጉም ታስገኛለች። ነፍስ ሦስት ባሕርያት አሏት፣ ነባቢነት ለባዊነትና ሕያውነት ሰው ነፍስ አልባ በሚሆንበት ጊዜ ስሙ ይለወጥና አስከሬን (እሬሳ) የሚል ስያሜ ይሰጠዋል። የነፍስ ደዌ ኃጢአት ነው። "ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች ኃጢአት ከአደገች በኋላ ሞትን ትወልዳልች" ያዕ ፩፥፲፭፤ ይህ ኃይለ ቃል የነፍስን ባሕርይና ግብር ግልጽ ያደርገዋል። ረቂቅ ነገር ግንኙነት የሚያደርገው ረቂቅ ከሆነ ነገር ጋር ነው። ረቂቅ ነፍስ ረቂቅ ከሆነ ባሕርይዋ ጋር ተመሣጥሮ ኃጢአት ተጠቂ ያደርጋታል። ኃልዮ ወደ ነቢብ፣ ነቢብ ደግሞ በሥጋ በኩል ወደ ገቢር ይደርሳል። የነፍስ ደዌ በአንደኛ ደረጃ ፍርሃት፤ ጭንቀት፤ ተስፋ መቁረጥና የመሳሰለው ነው። ይህ ዓይነቱ የነፍስ ደዌ ለሥጋ አካል በደም ብዛት በደም ግፊት በስኳር በመሳሰለው አጥቅቶ ለሞት ያደርሰዋል። ይህ ብቻ አይደለም በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የነፍስ ደዌ ክፉ ምኞት፤ ጥርጥር፤ ቅናት፤ ምቀኝነት፤ ንዴት፤ አለመርካትና ጥላቻ በእነዚህ ደዌዎች በመነሳሳት በሌላው ሕይወት ላይ የጭካኔ ተግባር ይፈጽማል፣ ለራሱም ሕይወት አይሳሳም። የአንደኛውና የሁለተኛው የዓለም ጦርነት

እንዲሁም በየጊዜው በየቀኑ በየዜና አውታሮች የሚሰሙ ግጭቶች ግድያዎች የነፍስ ደዌ ኃጢአት ውጤቶች ናቸው።

በተለይ በሀገራችን በአሁኑ ወቅት ከጥላቻ የኃጢአት ደዌ የተነሣ በትረ መንግሥቱን በጉልበት የጨበጠው ክፍል በወገኖቹ ላይ እየፈጸመ ያለው ጭካኔና ግፍ መግለጫ ቃላት እስከ አሁን አልተዘጋጀለትም (አልተበጀለትም)። ይህንንም እግዚአብሔር ለወሬ ነጋሪ እንደነ አቤሜሌክ ከሞት ያተረፋቸው እነ ኃብታሙ ምሥክሮች ናቸው። በአለፈው የገብር ጌር እሁድ በዝርወት የምትገኘው የርእሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ምዕመናንን "ሞቷል" ተብሎ የተጣለውንና እንደ አልአዛር እግዚአብሔር ያስነሳው አቶ ኃብታሙ አያሌውን ጎብኝተናል። በጉብኝታችን ወቅት የተመታ ቁስሉን የደቀቀ አካሉን ተመልክተናል፣ ሲሰሙት የሚሰቀጥጥና የሚዘገንን ከሀሊና በላይ ሲሰሙት ጆሮን ጭው የሚያደርግ በእሱና በመሰሎቹ የተፈጸመውንና እየተፈጸመ ያለውን ሲያጫውተን እራሳችንን መቆጣጠር ተስኖን እንደነበረ እናስታውሳለን። እግዚአብሔርን በማወቅ የመጀመርያዋ ሀገር፤ የሰው ልጅ የምድሩን ምርምር አጠናቆ ወደ ዓለመ ከዋክብት በተሸጋገረበት በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ግብረ አራዊት በሀገራችን እየተፈጸመ መሆኑ እጅግ የሚያሳፍርን የሚያሳዝን ነው። ይህ ሁሉ የነፍስ ደዌ ኃጢአት ውጤት እንደሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት ያረጋግጣሉ።

ለመሆኑ የነፍስ ደዌ አዳኝ አለው? ለመዳን አዳኝ ለፈለገ ሁሉ ፍቱን መድኃኒት አለው። በመጀመርያ ግን ባለ መድኃኒቱን መፈለግ ማወቅና ማግኘት ያስፈልጋል። እሱን ፈልጎ ለማወቅ አውቆ ለማግኘት በጣም ቀላል ነው። እንደ ዛሬው ጉጉል በአልታሰበበት ወቅት ለሁሉ የተገለጸ ነው። ያ አዳኝ ለዓለም መድኃኒት በመሆን ለምሥራቁም፣ ለምዕራቡ፣ ለሰሜኑና ለደቡቡም በሚታይ በቀራንዮ ኮረፍታ በወርቅ የደም ቀለም (በወርቀ ደሙ) በመስቀሉ ላይ ኑ ዳኑ የሚል ተጽፏል። የማንኛውም ቋንቋ ተናጋሪ ማንበብ፣ መስማትና ማወቅ ይችላል። ከዚህም ጋር የሚያዛቸውም መድኃኒቶችም ማንኛውንም የነፍስ ደዌ የሚፈውሱ ናቸው። እነርሱም እምነት፣ ተስፋ፣ ፍቅር፣ ይቅርታና ንስሐ ናቸው። እነዚህን በትዛዙ መሠረት የሚፈጽም ግለሰብ ቤተሰብና ማኅበረሰብ መጽሐፍ እንደሚለው "ልብሳቸውን በበጉ ደም ያጠቡና የአነጹ የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ቀረቡ፣ በመቅደሱ ውስጥም ቀንም ሌሊትም ያመሰግኑታል ያ በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው ያረፍባቸዋል፤ በእነሱ ላይም ያድራል። ከእንግዲህ አይታመሙም፤ አይራቡም፤ የፀሐይ ሐሩር አያገኛቸውም። በዙፋኑ ፊት ያለው በጉ ይጠብቃቸዋልና፤ ወደ ሕይወት ውኃ ምንጭም ይመራቸዋልና፤ እግዚአብሔርም እንባን ከዓይናቸው ያርቃል።" ራእ ፯፥፱-፲፯፤ በማለት ዘለዓለማዊውን አዳኝ ሕይወት ያረጋግጣል።

## በጠላት እጅ የወደቀ

በጠላት እጅ የሚወድቅ ግለሰብ ቤተሰብና ሀገርን የሚያጠቃልል ነው። ከአቅሙ በላይ

በሆነ ኃይል እጅ የወደቀ ግለሰብ ከወደቀበት አዳኝ ያስፈልገዋል። በወንጌሉ የዘለዓለም ሕይወትን ለመውረስ ለጠየቀው ወጣት ምን ቢያደርግ መዳን እንደሚገባው አስረዳው፤ መልሶ ወጣቱ ባልንጀራዬ ማነው ብሎ ጠየቀ፤ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሽፍቶች ደብድበው የጣሉትን እንዲያድን ኃላፊነት እንደ ሰጠው ታሪኩ ይናገራል።

በመቀጥልም ያን በሽፍታ ተደብድቦ የወደቀውን ሰው ካህኑም፤ ሌዋዊውም ማዳን ሲችሉ እንዳላየ አይተው ዝም ብለው እንደሄዱ ያመለክታል፤ ሳምራዊው ግን የመጀመርያውን እርዳታ ከአደረገለት በኋላ በአህያው ጭኖ ወደ ባለመድኃኒት አደረሰው፤ ለግለሰቡ አስፈላጊውን በእጁ ያለውን ከሰጠ በኋላ ተጨማሪ ወጪውን እንደሚልክለት ቃል እንደገባለት ታሪኩ ያረጋግጣል። ሉቃ ፲፥፴--፴፯፤ ዛሬ የሀገራችን ጋዜጠኞች እነ ተመስገን ደሳለኝ "እውነትን እውነት፣ ሐሰትን ሐሰት" ብለው ቢጽፉ ቢናገሩ በበርሐ ሽፍታ ወያኔ እጅ ተደብደበው ወደቀው በሲኦል እሥር ቤተ ተጥለዋል። የተገረፈ ጀርባቸውን የደቀቀ ሰውነታቸውን እያሳዩ የአዳኝ ያለህ፣ የወገን ያለህ እያሉ የሰቆቃው ድምጽ እያሰሙ ናቸው። ነገር ግን የኦርቶዶክሱ ፓትርያርክ፤ ጳጳስ፤ ካህንና ሰባኪ የፕርቴስታንቱ ፓስተር፤ መጋቢና ወንጌላዊ፤ በውስጥም በውጭም የአሉ የፖለቲካ አቀንቃኞች ጆሮ ዳባ ልበስ ብለዋል፤ ይህም ብቻ አይደለም ከመንግሥት (ከሕወሓት) ጋር ውህደት በመፍጠር ገራፊና አስገራፊ መሆናቸው ነው። በጥዝጣዜ ላይ ጥዝጣዜ እየጨመረ፣ ቁስላቸው አመርቅዞ በሞትና በሕይወት ላይ ይገኛሉ። ታድያ አዳኝ ወዴት አለ? "ውኃው አናቂ ስለቱ እባጭ" ሆኗልና። በዚህ ዘመን አዳኝ ሳምራዊውን እንዴት ማግኘት ይቻላል? ሸንበቆ ቢደገፉት ይጥላል፤ ቢመረኮዙት ይሰበራል፤ ዛሬ ሳምራዊውን ለማግኘት ከተደገፍንበት ሰብአዊ እምነታችን መላቀቅ ያስፈልጋል። ሰው አምነኸው ይከዳኃል፣ ተስፋ አድርገኸው ተስፋ ያስቆርጥኃል፣ እየሳቀ ያታልልኃል፣ ከጎንህ ነኝ ሲልህ ርቆ ታገኘዋለህ፤ ይደግፈኛል ስትል ውድቀትህን ያመቻቻል፤ስታጎርሰው ይነክስኃል። ይህ መሰሉ ሰው ለግለሰቡና ለማኅበረሰቡ ጠንቅ ነው።

በግለሰቦች የሚደርሰው ግድያ እስራት፣ እንግልት በእነሱ ብቻ የሚያቆም አይደለም፣ ቤተሰብንም የሚበክል ይሆናል። በአባወራው የሚተዳደሩ ህፃናት የትምሕርት እድላቸው ይቋረጣል፣ ከሞት ተርፈው ቢያድጉ ጉዳቱ ለኅብረተሰቡና ለሀገር ጠንቅ ይሆናሉ። በዚህ በዓለንበት ክፍለ ዘመን የአልተማረ ትውልድ "ካብ የማይገባ ድንጋይ ነው" ዓለምን እያናወጸ ያለ አይሲሲ የሚጠቀመው እንደዚህ በአልተማሩ ጉብሎች ነው። ማፍያም የሚባለው ከዚህ የተለየ አይደለም። የሁለተኛውን የዓለም ጦርነት ከአነሳሱት አንዱ ኢትዮጵያን የወረረው ሙሶሊኒ የዚህ ዓይነት ሰው እንደነበረ ነው ታሪክ ያረጋግጣል። ዛሬም ኢትዮጵያን የሚመሩት አብዛኞቹ የዚህ ዓይነቶች ናቸው። በአንድ በአባወራው ሥር የሚተዳደሩ ህፃናት ብቻ አይደሉም፣ በዕድሜ የገፉ በደዌ የተመቱ አረጋውያንና አረጋዊያት ወላጆች ጉሮሯቸው ይዘጋል፣ ለሞት ይዳረጋሉ። መጽሐፍ "እረኛውን ያዘው መንጋው ይበተናል" የሚለው ይህን የመሰለውን ነው። መንግሥት እየተጠቀመ ያለው የዚህ ዓይነቱን

ስልት ነው። ትውልድን በማቀጨጭ ዘርን በማጥፋት የተካነበት ነውና።

ይህንን ከመሰለው ደዌ አዳኙ ምንድነው? መልሱ የተፈጥሮን ህግ መጠበቅ ነው። ኢትዮጵያ ሀገራችን የተባበሩት መንግሥታት እንደተመሠረተ አባልነቷን ከአረጋገጡት ሀገሮች አንዷ ናት። የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር የመጀመርያውን ክፍል የያዘው የግለሰቦችን መብት መጠበቅ ላይ ያተኮረ ነው።እነዚህ የተፈጥሮ ህግጋት እያንዳንዱ ሀገር በህገ መንግሥቱ ሠፍረው ይነበባሉ። እግዚአብሔርም ሰውን ሲፈጥረው ከሌሎች ፍጥረታት አልቆ አክብሮ የራሱን እስትንፋስ አካፍሎ ዘለዓለማዊነትንና ነፃነትን አጎናጽፎ በፍጥረታት ላይ አምባሳደር አድርጎ የተሾመ ነው። ሰውም በተሰጠው አምላካዊ የተፈጥሮ ህግ በአካል በጉልበት ከእሱ የሚበልጡትን በማንበርከክ ዓለምን በመቆጣጠር ላይ ይገኛል። "ለሰብእ ፀሩ ሰብዓ ቤቱ" "የሰው ጠላቱ መሰሉ ቤተሰቡ" እንደሚባለው ከዚህ ዓይነት ጠላትነት ተላቅቆ የተፈጥሮን ህግ አክብሮ ከተጓዘ መድኃኒቱ እሱ ነው።

ሌላው ለመዳን አዳኝ የሚያስፈልገው ሀገርና ሕዝብ ነው። ሀገራችን ሕዝባችን እንደሌላ ሕዝብና ሀገር በዘይቤ አነጋገሮች ቢቀላለድም አንድነቱን ጠብቆ ለዘመናት የኖረ ነው። በርካታ የአፍሪካ ሀገራት በቅኝ ግዛት ሲያዙ ኢትዮጵያ ነፃነቷን ተጎናጽፋ የኖረችው በእግዚአብሔር ረዳትነትና በሕዝቡ አንድነት ነው። ለረዥም ዘመናት በዚህ ዓይነት የኖረውን ሕዝብ ሁሉም በየቋንቋ የሚነገረውን የዘይቤ አነጋገር የጥላቻ ውርሶች በትውልዱ እንዲቀጣጠል ክብሪት የሚለኩሱ አልታጡም ነበር። በተለይ ደግሞ አሁን የአለው መንግሥት ቂም በቀሉ አካል ገዝቶ ገዝፎ እንዲታይ በዘር ጥላቻ ገለጸው። አማራውን በኦሮሞው ላይ፣ ኦሮሞውን በአማራው ላይ አነሳሳው። አንድ ክፍለ ዘመን ወደ ኋላ ተመልሶ ምኒልክን ጡት ቆራጭ አድርጎ የጥላቻ ግንብ ገነባ። በዚህ ምክንያት ሕዝበ ኢትዮጵያ አንድነቱን ጠብቆ ለዘመናት የኖረውን ሆድ ጀርባ ሆነ፤ አንዱ ዘር በሌላው ዘር ላይ ጥላቻ አሳደረ። ይህ ለሀገሪቱ ትልቅ ውድቀት ነው። ለህዝቡ ደግሞ ማንም ጠላት ሳይነሳበት እራሱን በራሱ ገመድ በአንገቱ እያስገባ ለትውልድ የሚተላለፍ ገዳይ ደዌ እየተሰራጨ ነው። በዚህ ደዌ የአለቀና እያለቀ የአለው ህዝብ በቀላል የሚገመት አይደለም። አሁንም በዚህ በዘር በሽታ ተጠቅተው በጣር ላይ የአሉ ብዙ ናቸው። ይህም ከምዕራቡ ዓለም ወደ ሀገራችን የገባ ደዌ ነው። ፈጥኖ መድኃኒት ከአልተገኘለት ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ህልውና አልባ እንዳትሆን እሰጋለሁ።

መጽሐፍ "ኩን ጠቢበ በዱከ" "በጠላትህ እወቅበት" ይላልና፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀገሩን ለማዳን ማወቅ፣ ማስተዋል ያስፈልገዋል። መድኃኒቱ በእጁ ላይ ነው። ምንድነው ትለኝ እንደሆነ? በመጀመርያ መለኮታዊውን ኃይለ ቃል እጥቀስልኃለሁ። "እርስ በርሱ የተከፋፈለ መንግሥት ሁሉ ይወድቃል እርስ በርሱ የተከፋፈለ ከተማ ወይም ቤት አይጸናም"። ማቴ ፲፪፥፳፭፤ ስለነገረ ምጽዓቱ ምልክት ሲናገርም "መንግሥት በመንግሥት ላይ ሕዝብ በሕዝብ ላይ ይነሳል" ይላል። መለያየቱ የመንግሥት ውድቀት፤ የሕዝብ አለመረጋጋትና የሀገር አለመጽናት ከሆነ፤ ምጽአትን የአለጊዜው እያወጅን እንደሆነ የምንጓዝበት ሂደት

ያረጋግጣል። “ሳይቃጠል በቅጠል” እንደሚባለው መድኃኒቱ በእጃችን አለ፤ እሱም ልባዊ እርቅና ልባዊ ይቅርታ ነው። መንግሥት ከሕዝብ፣ ሕዝብ ከመንግሥት፣ ሕዝብ ከሕዝብ በቂም በበቀል ከተመታበት በሽታ ለመዳን ብሔራዊ እርቅ፣ ብሔራዊ ይቅርታ መምጣት አለበት። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ፤ እቅድና ዓላማ እንደ እኔም እምነት አማራጭ የሌለው ፍጹም ፈውስ ሰጪ መድኃኒት ይህ ብቻ ነው።

በተጨምሪም ወደ ሩቁ ዘመን ጉዳት፣ ዘመነ ግራኝ መሐመድና ዘመነ መሳፍንት ሳልሄድ የቅርቡ የአርባ ዓመታት የመጠፋፋት ዘመናት ምሥክሮቻችን ናቸው። በዚህ ሁሉ ሂደት ማንም ተጠቃሚ አልነበረም። ትርፋችን ኪሳራ ሆኖብናል። እግዚአብሔርን ማጣቱ፤ ሕዝብ መጨፍጨፉና ማስጨፍጨፉ፣ ሀገር መገንጠሉና ማስገንጠሉ፣ ድንበር ማስደፈሩና ወደብ አልባነቱ ጉልህ ምሥክሮች ናቸው። ለዚህ ነው የነበረንን ለማስመለስ አሁን የአለንን ለመጠበቅ ብሔራዊ እርቅና ብሔራዊ ይቅርታ ያስፈልጋል የምለው። እንዴት ይመጣል? ወደፊት እመጣበታሁ። የዘንድሮው እንኳን ለጌታችን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ትንሣኤ አደረሳችሁ መልእክቴ ይህ ይሆናል። የክርስቶስን ትንሣኤ ስናስብ ከዚያ በፊት የነበረውን ሰሙነ ሕማማቱንና ስቅለቱን ልናስተውል ይገባል። ክርስቶስ ለናቁት፤ ምራቃቸውን ለተፉበት፤ መስቀል አሸክመው ለአንገላቱት፤ ለገረፉትና ለሰቀሉት መስቀል ላይ ሆኖ ለዓለም ሕዝብ ያስተላለፈው የኑዛዜ መልእክት “አባት ሆይ የሚሠሩትን አያውቁምና ይቅር በላቸው” የሚል ነበር። ዛሬ በውስጥም፣ በውጪም ያለው ኢትዮጵያዊ ጥቂት በጣት ከሚቆጠር በቀር የሚበልጠው የሚሠራውንና የሚናገረውን አያውቅም። መንግሥት ለምን መንግሥት እንደተባለ አያውቅም ጳጳሳት ካህናትና ሰባክያን ለምን እንደተሰየሙ ማንን እንደሚያገለግሉ አያውቁም። ክርስቶስ የይቅርታ ኑዛዜ ያስተላለፈው የምንሠራውን ለማናውቀው ለእኛ ነውና። በዚህ መለኮታዊ ኑዛዜ መሠረት ለይቅርታና ለእርቅ እንነሣ። የሀገር ትንሣኤ የሕዝብ አንድነት የሚመጣበት መድኃኒቱ ይህ ብቻ ነው። ልባዊ ይቅርታ ልባዊ እርቅ ይምጣ። ብሔራዊ እርቅ ብሔራዊ ይቅርታ ይታወጅ። ዕርቅ፤ ዕርቅ፤ እርቅ። ይቅርታ፤ ይቅርታ፤ ይቅርታ። “ለመዳን አዳኛችን” ይህ ብቻ ነውና። አሜን።

**እንኳን ለበዓለ ትንሣኤው አደረሳችሁ፣ አደረሰን!**

ሚያዝያ ፲ ቀን ፳፻፱

ሊቀ ማእምራን ቀሲስ ዶክተር አማረ ካሣዬ

የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳዳሪ